# የመማሪያ መጻሕፍት ሽያጭና
# የሚያጋጥሙት ችግሮች ።

ከዘውድነህ ይምታቱ

## መግቢያ

ትምህርት በኢትዮጵያ ከተመሠረተ ረጅም ጊዜው ነው ። ቢሆንም የተማሩ ኢትዮጵያውያን ሐሳባቸውን በጽሑፍ ማስፈርና የተጻፉ ነገሮችን ማንበብ እምብዛም አያዘወትሩም ነበር ።

ጥንት ከነበሩት ጽሑፎች ብዙዎቹ በግዕዝ የተጻፉ ነበሩ ። ስለዚህም ለጸሎትና ለመንፈሳዊ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር እነዚህን ጽሑፎች ለማንበብ ብዙ አባባይ ነገር አልነበረም ። አንዳንዶቹም ንባብ የሚችሉት ግዕዙን ሲያነብቡ በሚደረገው የማጥበቅ ፤ የማላላትና የመሳሰሉትም ስልቶች ብዙ እንደሚገድፉ ይነገራል ።

ብዙ የተጻፉ ነገሮችን ካለማንበብ የተነሣም በጽሑፎች የሠፈሩ ነገሮችን ሁሉ ያለጥርጣሬ የመቀበልና የማመን ዝንባሌ በብዙ ኢትዮጵያውያን ላይ አሁን እንኳን ይታያል ።

በጽሑፍ የሠፈሩ ነገሮች ሁሉ (በመጽሐፍ ቅዱስና በቁራን ተመርኩዘው) መንፈሳውያን ነበሩ ። የመንግሥት አዋጆች እንኳን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በገበያና በሌሎችም የሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎችና በርኖስ በሽመል ብጤ ላይ ሰቅሎና "አዋጅ ፤ አዋጅ . . ." የሚለውን ቃል በረጅሙ ለፍፎ ሕዝቡ ሊሰማ ወደሚችለው ቦታ ሲቀርብ በቃል ይነገሩ ነበር እንጂ ፤ የጽሑፍ አዋጅ እምብዛም አልነበር ። በመንግሥታዊና በሌሎች ከመንፈሳዊነት ውጪ በሆኑ ነገሮች ይሰጥ የነበሩት የጽሑፍ መረጃዎች በጣም የተወሰኑና ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ የተባሉ ነበሩ ። በመንፈሳዊው በኩልም እንደዳዊት ያለው ትምህርት በቃል ይጠና ነበር እንጂ ፤ በመጻፍና በማንበብ በኩል ያለው ሙከራ እምብዛም አልነበር ።

የጸሐፊዎችንና የአንባቢዎችን ብዛት የዘመኑ ትምህርት አሻሽሎታል ። ቢሆንም እላይ እንደጠቀስኩት ኢትዮጵያውያን ብዙ አንባቢዎች አይደሉም ። ተማሩ የተባሉት ኢትዮጵያውያን አዘውትሮ የማንበብና የመጻፍ ልምድ ያንሳቸዋል ። አንዳንዶቹ ለምን እንደማያነብቡ ሲጠየቁ ፤ በቂ የሚነበቡ ነገሮች አለመኖራቸውንና ጊዜም አለማግኘታቸውን ያወሣሉ ።

አንዳንድ ወጣቶች ምናልባትም ዓዋቂዎችም ጭምር ፤ መጻሕፍት ተሸክመው የሚሄዱት ለወግና ለይስሙላ ያህል ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል ። በዛሬ ዘመን መጻሕፍት የሚገዙትና የሚነበቡትም በውስጣቸው ባሉት ሃሳቦች ለመጠቀም ሲሆን ፤ በጥንት አስተሳሰብ ግን አንዳንድ መጻሕፍት ከመነበባቸው ሌላ ተፈላጊ

# የመማሪያ መጻሕፍት ሽያጭና የሚያጋጥሙት ችግሮች ።

ከዘውድነህ ይምታቱ

## መግቢያ

ትምህርት በኢትዮጵያ ከተመሠረተ ረጅም ጊዜው ነው ። ቢሆንም የተማሩ ኢትዮጵያውያን ሐሳባቸውን በጽሑፍ ማስፈርና የተጻፉ ነገሮችን ማንበብ እምብዛም አያዘወትሩም ነበር ።

ጥንት ከነበሩት ጽሑፎች ብዙዎቹ በግዕዝ የተጻፉ ነበሩ ። ስለዚህም ለጸሎትና ለመንፈሳዊ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር እነዚህን ጽሑፎች ለማንበብ ብዙ አባባይ ነገር አልነበረም ። አንዳንዶቹም ንባብ የሚችሉት ግዕዙን ሲያነብቡ በሚደረገው የማጥበቅ ፤ የማላላትና የመሳሰሉትም ስልቶች ብዙ እንደሚገድፉ ይነገራል ።

ብዙ የተጻፉ ነገሮችን ካለማንበብ የተነሣም በጽሑፎች የሠፈሩ ነገሮችን ሁሉ ያለጥርጣሬ የመቀበልና የማመን ዝንባሌ በብዙ ኢትዮጵያውያን ላይ አሁን እንኳን ይታያል ።

በጽሑፍ የሠፈሩ ነገሮች ሁሉ (በመጽሐፍ ቅዱስና በቁራን ተመርኩዘው) መንፈሳውያን ነበሩ ። የመንግሥት አዋጆች እንኳን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በገበያና በሌሎችም የሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎችና በርኖስ በሸመል ብጤ ላይ ሰቅሎና "አዋጅ ፤ አዋጅ . . ." የሚለውን ቃል በረጅሙ ለፍፎ ሕዝቡ ሊሰማ ወደሚችለው ቦታ ሲቀርብ በቃል ይነገሩ ነበር እንጂ ፤ የጽሑፍ አዋጅ እምብዛም አልነበር ። በመንግሥታዊና በሌሎች ከመንፈሳዊነት ውጪ በሆኑ ነገሮች ይሰጥ የነበሩት የጽሑፍ መረጃዎች በጣም የተወሰኑና ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ የተባሉ ነበሩ ። በመንፈሳዊው በኩልም እንደዳዊት ያለው ትምህርት በቃል ይጠና ነበር እንጂ ፤ በመጻፍና በማንበብ በኩል ያለው ሙከራ እምብዛም አልነበር ።

የጸሐፊዎችንና የአንባቢዎችን ብዛት የዘመኑ ትምህርት አሻሽሎታል ። ቢሆንም እላይ እንደጠቀስኩት ኢትዮጵያውያን ብዙ አንባቢዎች አይደሉም ። ተማሩ የተባሉት ኢትዮጵያውያን አዘውትሮ የማንበብና የመጻፍ ልምድ ያንሳቸዋል ። አንዳንዶቹ ለምን እንደማያነብቡ ሲጠየቁ ፤ በቂ የሚነበቡ ነገሮች አለመኖራቸውንና ጊዜም አለማግኘታቸውን ያወሣሉ ።

አንዳንድ ወጣቶች ምናልባትም ዓዋቂዎችም ጭምር ፤ መጻሕፍት ተሸክመው የሚሄዱት ለወግና ለይስሙላ ያህል ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል ። በዛሬ ዘመን መጻሕፍት የሚገዙትና የሚነበቡትም በውስጣቸው ባሉት ሃሳቦች ለመጠቀም ሲሆን ፤ በጥንት አስተሳሰብ ግን አንዳንድ መጻሕፍት ከመነበባቸው ሌላ ተፈላጊ

ነት አላቸው ። ይኸውም ለሚያቃኙቸው ሰዎች አጋንንትን ማራቂያ መሆናቸው ነው ። በዚህ ረገድ ለምሳሌ ብዙዎቹ ሰዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ተንተርሰው ይተኛሉ ። በዚህ አስተሳሰብ ሰነፍ ተማሪም ታሪክና ምሳሌን ተንተርሶ በማደር ስንፍናን አርቄ የሚቀጥለውን ቀን ፈተና አልፋለሁ ብሎ ቢጓጓ ፤ ተበልቶ አንጀት እንደማይደርስ እንጀራ ይሆንበታል ። መጻሕፍት ለንባብና በውስጣቸው ያለውን ሐሳብ አንብቦ ለመገልገል እንጂ ለሌላ ነገር አይውሉም ። ቢሆንም ሁሉንም መጻሕፍት እኩል በማንበብ በውስጣቸው ያለውን ሐሳብ እኩል መጠንቀቅ አይቻልም ። አንዳንድ መጻሕፍት ከበድ ያሉ ሐሳቦች አሏቸው ፤ በጠቅላላ አነጋገር ግን ልብወለድ ታሪኮች ለአንባቢያቸው ቀላል ናቸው ። ይህም ሲባል አንዳንዶቹ ለምሳሌ እንደ ራስሜላስ ያሉት ከባድ ከሚባሉት መጻሕፍት እኩል ይከብዳሉ ።

<u>የመማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት ፤</u>

በዘመኑ ት/ቤት ፤ ተማሪዎች የሚማሩትና መምህራን የሚያስተምሩት አንድነት ተወስዶ ሲመዘን የሚገኘው ውጤት ሥርዓተ ትምህርት "ካሪኩለም" ይባላል ።

መጻሕፍት ለሥርዓተ ትምህርት ጥሩ ውጤትና ጥንካሬም ዓይነተኛ ድጋፍ ናቸው ። በዘመኑ ት/ቤት የሚገኙ መጻሕፍት አራት ዓይነት ናቸው ።

ሀ/ ማስተማሪያ መጻሕፍት በዓመቱ መጨረሻ ተማሪው ሊያውቃቸው የሚገባ ፤

ለ/ ተጨማሪ መጻሕፍት ለማስተማሪያ መጻሕፍት ተጨማሪ ሆነው የሚያገለግሉ ፤

ሐ/ መረጃ መጻሕፍት መዝገበ ቃላትን የመሳሰሉት

መ/ የግል ንባብ መጻሕፍት ተማሪው በግል ጊዜው እንዲያነብባቸው የተመደቡ ። (ልብወለድ ፤ መጽሔትና ጋዜጦችም)

አንዳንድ ተማሪዎችና መምህራን የክፍሉን ትምህርት ለማጠናቀቅ የማጀሩ
ወይንም የማስተማሪያ መጻሕፍትን በማንበብና በማስነበብ ብቻ ይወሰናሉ ።
ዓይነቱ የመማርና የማስተማር ልምድ ያልተሟላ ድርጊት ይባላል ። እርግ
ምንት ክፍለ ጊዜና በየክፍሉም ያሉት ተማሪዎች ብዛት የመምህራንን
ማር ኃይል ይቀንሳሉ ። ቢሆንም የዘመኑን የማስተማር ዘዴ የተማሩ መሳ
እንደዚህ ዓይነቱን ችግር ሊቋቋሙት ይገባል የመማሪያ መጻሕፍትንና
ቹን የትምህርት መሣሪያዎች ፍቱንነት ሲያስረዳ የትምህርትና ሥነ ጥበ
ስቴር እንዲህ ይላል ። "ከጠላት ጋር የሚዋጋ ወታደር ፍቱን መሣሪያ
ድል አድራጊነቱ እንደሚያጠራጥር ሁሉ ፤ መምህርም ፍቱን የማስተማሪያ
ማሪያ መሣሪያዎች ካልያዘ ከድንቁርና ጋር በሚያደርገው ትግል አሸናፊነቱ በእ
ርግጥ አይታወቅም ።"

ጥሩ ጥሩ የትምህርት መሣሪያዎችን ማግኘት ፤ ምርጥ መምህራንን ከማግኘት ባይወዳደርም ፤ መደበኛ የማስተማሪያ ዕቃዎች የሌሏቸው የምርጥ መምህራን ሥራ እንካሣ ይሆናል ።

መጻሕፍት ፣ ጥቁር ሠሌዳዎች ፣ ካርታዎችና ቻርቶች በማንኛውም ትምህርት ቤት ሊገኙ የሚያስፈልጉ መሠረታዊ የትምህርት መሣሪያዎች ናቸው ። በዘመኑ የመምህራን ማሠልጠኛ ትምህርት ቤቶች የሚሠለጥኑ መምህራን ሁሉ የትምህ ርት መሣሪያዎችን ጥቅምና አገልግሎት ከማስተማር ዘዴዎች ጋር የሚማሩት ስለዚህ ነው ።

የመማሪያ መጻሕፍት ባንድ አታሚ ብቻ መታተማቸው ለትምህርት ሚኒስ ቴር ልዩ ልዩ ችግሮችን ፈጥሮ ነበር ። ይኸውም መጻሕፍቱ ባንድ ቦታ ብቻ በመ ታተማቸው ዋጋቸው አለመጠን ውድ ሲሆን የሥራ ጥራትና ቅልጥፍናም አልነ በራቸውም የሚል ሃሜት ይነፍስ ነበር ። ከጥቂት ዓመታት ጀምሮ ግን በኢትዮ ጵያ ያሉት ትላልቅ ማተሚያ ቤቶች በሙሉ ጨረታ ስለሚወስዱ ምንም ቀድሞ የት/ሚኒስቴር ደንበኛ የነበረው ማተሚያ ቤት በዋጋ ቅናሽና በሥራ ቅልጥፍና አሁንም ቅድሚያን ይዞ ቢገኝ ፣ የነበረው ሃሜት አሁን አይሰማም ።

የመጻሕፍት በጊዜው ታትመው የመቅረብ ጉዳይ ካለፉት ዓመቶች ይልቅ በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም. እና በ፲፱፻፷፬ ዓ.ም. በጣም ተሻሻለ ይባላል ። ሆኖም የተገልጋዮችን ፍላጐት ለማርካት ሥራው አሁንም ብዙ ይቀረዋል ።

እንደተደረሰበትም ማተሚያ ቤቶች በሰዓቱ መጻሕፍቱን የማያደርሱት አን ዳንዴ የጽሑፎች በሰዓቱ አለመቅረብ ወይንም ደግሞ መጻሕፍቱ እንዲደርሱ የሚ ፈለግበት ጊዜ ቀደም ብሎ ስለማይገለጽ ነው ።

መጻሕፍትን ለአራትና ለአምስት ዓመት በቅድሚያ አሳትሞ ማስቀመጥ ምና ልባት መልካም ይመስላል ። በዋጋም በኩል በጣም ይቀንሳል ። ነገር ግን እስካ ሁን በት/ሚኒስቴር በኩል ያለው ችግር ፣ የሥርዓተ ትምህርቱ በየዘመኑ መለዋ ወጥና ለታተሙት መጻሕፍት ማከማቻ ትልልቅ መጋዘኖች ማጣት ናቸው ።

የመማሪያ መጻሕፍት አሻሻጥ ደንብና ሥርዓት ፣

በ፲፱፻፷፪ ዓ.ም. የተደረገው የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ባለሥልጣ ኖችን የትምህርት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጆች ጉባዔ ስለመጻሕፍት ሽያጭ የተረ ቀቀውን ደንብ ሲያጸድቅ ፣ የሚከተሉትን ዘርዝሮአል ፣

፩ኛ/ በልዩ ልዩ ጠ/ግዛቶችና ት/ ቤቶች የመማሪያ መጻሕፍት በነፃ በኪራ ይና በሽያጭ በመታደላቸውና አንድ ዓይነት ደንብ ባለመኖሩ ለትምህርቱ አስተ ዳደር ችግር ፈጥሮ እንደነበርና ፣

፪/ በተለያዩ ጊዜአት የወጡትም የተለያዩ ደንቦች መጻሕፍቱ በት/ቤቶች እንደልብ እንዳይገኙ ዓይነተኛ ምክንያት እንደሆኑ አትቶአል ። ስለወደፊቱም የመ ማሪያ መጻሕፍት ግልጋሎት ፣

ሀ/ መጻሕፍት ለመግዛት ለማይችሉ በት/ቤቱ መጻሕፍት ወይም በሌላ አማ ካይ ቦታ እንዲደረጉላቸው ፣

ለ/ ሕዝቡ ስለመጻሕፍት ግዢ እንዲገባው በልዩ ልዩ ዘዴ ገለጻ እንዲደረግ ለትም መምሪያ እንዲሰጥ ሲወስን ፣ የቀድሞውን ደንብ ለማሻርና መጪውንም በሥራ ላይ ለማዋል ጉባዔው ፣

— መጻሕፍት የሚሸጡት በዲሬክተሩ አማካይነት እንዲሆን

— የመጻሕፍቱ ሺያጭ ገቢ ከመሥሪያ ቤቱ በተዘጋጀው የገቢ ደረሰኝ ብቻ እንዲሰበሰብ

— ለሚቀጥለው የት/ዘመን የሚፈለጉት መጻሕፍት ዝርዝር ከታኅሣሥ ፴ በፊት ለዋናው መሥሪያ ቤት እንዲደርስ

— የመጻሕፍቱን ገቢ ገንዘብ ፤ በጠ/ግዛትና በአውራጃው ከተሞች ያሉት ት/ቤቶች ዕለቱን ፤ በገጠር ያሉት ት/ቤቶች ደግሞ በወሩ መጨረሻ እንዲያስረክቡ ፤ ጠይቋል ።

፫/ በየጠቅላይ ግዛቱ ላሉት የሚሲዮን ት/ቤቶች ኃላፊዎቻቸው ከአዲስ አበባ በቀጥታ እንዲገዙላቸውና መጻሕፍት ለነዚህ ት/ቤቶች ከጠ/ግዛቶች በድጋሚ እንዳይሸጡ ጉባዔው ሲከለክል ፤ የግልና የቤተ ክህነት ት/ቤቶች ግን ከየጠ/ግዛ ቶች እንዲገዙ አሳስቧል ።

<u>የመማሪያ መጻሕፍት ሽያጭና ችግር ፤</u>

ከላይ እንደተጠቀሰው የመማሪያ መጻሕፍት በሽያጭ በየትምህርት ደረጃው ካሉት ሕፃናት እጅ እስኪገቡ ድረስ ብዙ ችግር ያጋጥማል ። የሆነው ሆኖ በትም ህርት ሚኒስቴርና በማተሚያ ቤቶች በኩል ያሉት ችግሮች በቅርብ የሚቀነሱና የሚወገዱ ሲሆኑ መጻሕፍት ከዋናው መሥሪያ ቤት ወጥተው በተገልጋዮቹ ተማ ሪዎች እጅ እስኪገቡና ከዚያም በኋላ ቢሆን ብርቱ ጥንቃቄ ካልተደረገ የትም ህርቱ ሥራ ፈሩን ይለቅ ይሆናል ። በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም. በቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ የትም ህርት ፋኩልቲ በተደረገው የክረምት ኮርስ ከመጡት መምህራንና ከዚያም በኋላ ከአንዳንድ የት/ቤት ዲሬክተሮች ፤ አስተማሪዎችና ተማሪዎችም ጋር በተደረገው ውይይት መጻሕፍትን በመግዛትና በመሸጥ የሚከተሉት ችግሮች እንደሚያጋ ጥሙ ተጠቅሷል ። እነዚህ ችግሮች በተማሪዎች ፤ በወላጆች ፤ በአስተማሪዎችና በዲ ሬክተሮች በኩል ያሉና በነሱውም የሚወገዱ ይመስላሉ ። ከችግሮቹም በከፊል የሚ ከተሉት ናቸው ።

፩/ ብዙ ወላጆች ማንበብ ስለማይችሉ ፤ ልጆቻቸው የመጻሕፍቱን ዋጋ ከፍ አድርገው በመንገር በርከት ያለ ገንዘብ ይቀበሉና ከመጻሕፍቱ ዋጋ የተረፈውን ለሌላ ጉዳይ ያውላሉ ። ጥቂቶቹም ልጆች የገዙት መጻሕፍት ለሌሎች ተማሪዎች በቅናሽ ዋጋ ሸጠውና ጠፋብን ብለው ወላጆቻቸውን በድጋሚ ሌላ መጻሕፍት ያስገዛሉ ።

፪/ አልፎ አልፎ መምህራንና ዲሬክተሮች አንዳንድ መጻሕፍት በውሰት ወስደው ዓመቱን ከሠሩባቸው በኋላ እነዚህኑ መጻሕፍት ለሌሎች ተማሪዎች በሚቀጥለው ዓመት ስለሚሸጡላቸው በወላጆች ዘንድ ቅሬታን ፈጥሮአል ።

፫/ ጥቂት መምህራን እንዲሸጡ የተረከቡትን መጻሕፍት ዋጋ በአጋጣሚ ምክንያት ገቢ ሳያደርጉ በመቅረታቸው ለዲሬክተሮች የአስተዳደር ሸክም ጨም ረዋል ። አንዳንዶቹም በነጭ ወረቀት ከተማሪዎች ገንዘብ ይሰበስቡና በካርኔ የሚ ያሰፍሩት በኋላ ስለሆነ ፤ ደረሰኝም ለተማሪዎች ስለማይሰጡ መምህራኑ መጻሕ ፍቱን ከተተመነባቸው ዋጋዎች በላይ ይሸጣሉ የሚል ሃሜት አስከትሎአል ።

በመጻሕፍቱ ላይ ዋጋቸውን መጻፉ ብዙውን የዚህ ዓይነት ችግር አስወግዷል ይባ
ላል ። ግን ራቅ ባሉት ቦታዎች ያሉ ጥቂት ባለጌ መምህራን የትራንስፖርትና የመ
ሳሰሉ ምክንያቶችን በማከል መጻሕፍቱን ከዋጋቸው በላይ ከመሸጥ አልተቆጠ
ቡም ። በዚህ ዓይነቱ ሃሜት አይብዛ እንጂ ዲሬክተሮችም ይታማሉ ።

፬/ ለየገጠሩ የሚላኩት መጻሕፍት በአህያ ጀርባ ስለሚደርሱ ብዙዎቹ ተጎ
ሳቁለውና ግልጋሎታቸው ተቀንሶ ይደርሳሉ ። አንዳንድ የገጠር ት/ቤቶች እነዚ
ህን ችግሮች የእንጨትና የቆሮቆር ሳጥኖች በማሠራት በመጠኑ ቀንሰዋል ይባ
ላል ። ከዚህ ጋር ተያይዞ ያለው ችግር የዕቃ ግምጃ ቤቶችና ሠራተኞቻቸው ለሥ
ራው ብቁ አለመሆን ነው ። ባንዳንድ ትምህርት ቤቶች እንደታየው ለመጻሕፍትና
ለሌሎችም የማስተማሪያ ዕቃዎች የሚመደቡት ክፍሎች ጽዳትና መከባከብ ያን
ሳቸዋል ። ቤቱ አይጥ የሚገባበት ፤ ዝናብ የሚያፈስስበት ወይም መደርደሪያ ከቶ
የሌለው ይሆንና ለመጻሕፍት ጉዳት ምክንያት ይሆናል ።

ለንብረት ሐላፊ ሆኖ የሚመደበውም ሰው በማስተማር ችሎታው ሕፃናትን
ሊያረካ ባለመቻሉ ፤ ወይም ለረጅም ዘመን በማስተማር የቆየ ፤ ወይም ማስተማር
አልወድድም ባይ እንጂ መጻሕፍትን በሚገባ የመያዝ ምንም ዓይነት ትምህርት
ያልተሰጠው ፤ የወይዘሮ አንጀሊና ማንጎን "አታንገላቱኝ" ግጥም ያላነበበ ፤ የት
ኞዎቹ መጻሕፍት ለማንኛው ክፍል እንደሚሆኑ ሊያውቅ የማይጨነቅ ፤ ከት/ሚኒ
ስቴር የሚተላለፉትንም የመጻሕፍት አሻሻጥ ደንቦች ጠንቅቆ ያላወቀ ይሆናል ።
የመጻሕፍቱን ሽያጭ ገንዘብ በሰዓቱ ገቢ ባለማድረግም ገንዘቡን የሚነግዱበት
ወይም አጥፍተው በክስ የሚገኙና የሌሎችንም ትምህርት ቤቶች ጥሩ ስም የሚያ
ጠፉ እንዳሉ ተወስቷል ።

፭/ በቂ መጻሕፍት በሰዓቱ ለት/ ቤቶች ላለመድረሳቸው የት/ሚኒስቴር ባለ
ሥልጣኖች የሚሰጡት ምክንያት ባለፉት ዓመቶች ለሺያጭ የተላኩት መጻሕ
ፍት ገንዘብ በሰዓቱ ባለመድረሱ ነው ፤ በቂ መጻሕፍት ላለመላካቸውም ሲያስረዱ፤
መጻሕፍት የሚላኩት ት/ቤቶች በላኩት የተማሪዎች ብዛት መሠረት ነው ይላሉ።

ያም ሆነ ይህ በዚህ ረገድ የተጠቀሱትን ችግሮች ለወደፊቱ ለማቃለል ልዩ
ዘዴዎች እንዳሉአቸው በት/ሚኒስቴር የዚህ ክፍል ሹማምንት ይናገራሉ ።

አንዳንድ ጊዜ መጻሕፍት ለተማሪዎች የማይደርሱት ከዋናው መሥሪያ ቤትና
ማተሚያ ቤቶች ጉድለት ሳይሆን በጠቅላይ ግዛት ፤ በአውራጃና በት/ቤቶች
ረጃ ምክንያት እንደሆነ ታውቋል ። ባለፈው ዓመት ለምሳሌ ፤ የአዲስ አበባ ት/
ቤቶች ከሌሎች ጠ/ግዛቶች ሁሉ ወደ ኋላ ቀርቶ የነበረው በጠ/ ግዛቱና በአንዳ
ንድ ት/ቤቶች ጉድለት እንደሆነ ይነገራል ።

፮/ በአዲስ አበባና በመሳሰሉት ከተሞች ባሉት የግል ት/ቤቶች የሚማሩት
ሕፃናት ገንዘብ ከፍለው መማራቸው አነሳቸውና መጻሕፍትን በሰዓቱ እንዳይገዙ
ት/ቤቶች ገንዘብ በቅድሚያ ካልከፈሉ መጻሕፍት አይሰጣቸውም የሚለው አሠ
ራር በጣም አሳዛኝ ነው ። ይህም አድራጐት ወደፊት የሚቀጥል ከሆነ ብዙ ወላ
ጆችንና ምሁራንን ማስቈጣቱ አይቀርም ።

የጠ/ግዛት ት/ቤቶች የእነዚህን ት/ቤቶች መኖር ካወቁ በጠ/ግዛታቸው መጻ
ሕፍት ለተማሪዎች እንዲደርሱ ማድረግ ግዴታቸው ሊሆን ይገባል ።

፯/ ስለመጻሕፍት ሽያጭ ችግር በሚተችበት ጊዜ መጻሕፍትን ለመግዛት ስለማይችሉ ተማሪዎች ሳይጠቀሱ ማለፍ አግባብ አይሆንም ። መጻሕፍት ለተማሪዎች እንዲሸጡ በተወሰነ ጊዜ ለመግዛት ለማይችሉ ልጆች መጻሕፍቱ በቤተ መጻሕፍት ተቀምጠው ከዚያ በውሰት እንዲያነብቡአቸው የሚል የት/ሚኒስቴር ደንብ አለ ። ነገር ግን ብዛት ያላቸው ት/ቤቶች ቤተመጻሕፍት ከቶ የሉአቸውም ። ቤተ መጻሕፍት ባሏቸው አንዳንድ ት/ቤቶች እንኳን ሌሎች የውጭ አገር መጻሕፍት በብዛት ሲኖሩ ተማሪዎች የሚፈልጉአቸው ግን አልተገኙም ። ለዚህ አድራጎት የቤተ መጻሕፍቱ አላፊዎች ደግሞ የማስተማሪያ መጻሕፍትን በቤተ መጻሕፍት ላለማኖራቸው የሚሰጡት ምክንያት "እነዚህን (የማስተማሪያ) መጻሕፍት ተማሪዎች ቢሰርቋቸው ሃላፊነት ስለሚያመጣ በዚህ ፍርሃት ነው የሚል ነው ።"

ሆኖም ብዙዎቹ ተማሪዎች መጻሕፍቱን ስለሚገዙና የማይገዙት ከጓደኞቻቸው ስለሚዋሱ የደንቡን ከሥራ ላይ አለመዋል አወሳሁ እንጂ በተማሪዎች በኩል ብዙም ችግር አይሰማም ።

፰/ በሥርዓተ ትምህርቱ ላይ የሚጠቀሱት መጻሕፍት ለሺያጭ (በት/ቤቶች) አለመቅረባቸው ወይም በሰዓቱ ከመስከረም ጀምሮ በተማሪዎች እጅ አለመግባታቸው አንድ ትልቅ ችግር ነው ። አንዳንድ ጊዜ ከሥርዓተ ትምህርቱ የተጠቀሱት ወይም ለአንድ የተወሰነ ደረጃ የሚታዘዙት መጻሕፍት ለስድስትና ለሰባት ወሮች ወይንም ለዓመቱም የማይደርሱ ይሆናል ። ምንም ይህን የመሳሰሉት ችግሮች ወደፊት ይቃለላሉ ቢባልም በአሁኑ ጊዜ እንደችግር ይወሰዳሉ ።

፱/ መጻሕፍትን ለመግዛትና ለሌላም የትምህርት ጉዳይ ገንዘብ ማውጣት በኢትዮጵያ የዘመኑ ትምህርት ቤቶች የተለመደ አይደለም ። ስለዚህም ተማሮች መጻሕፍት እንዲገዙ ሲነገራቸው ገንዘቡን አምጥተው ወዲያውኑ (ዕለቱን) ፡ ስለማይገዙ ይህን ጉዳይ ለሚያስፈጽሙ መምህራን ችግር ነው ። መጻሕፍት በንብረት ክፍል ኃላፊው ብቻ እንዳይሸጡ የዚህ ዓይነቱ ሥራ የት/ቤቶች ከመከፈታቸው በፊት ስለማይጀመር ት/ቤት ከተከፈተ በኋላ መጻሕፍትን ባንድ ሰው ብቻ ማደሉ ብዙ ጊዜ ይወስዳል ። መምህራኑ ደግሞ ከንብረት ክፍል ኃላፊው የተረከቡአቸውን መጻሕፍት ተማሪዎቹ ወዲያው ስለማይገዙአቸውና ያልተሸጡትን መጻሕፍት እስኪሸጡ የሚያሳርፉበት ቦታ ስለማይኖራቸው ብዙ ችግር አለ ። አን
ዳንድ መምህራን ችግሩን ለማቃለል መጻሕፍቱን ወደ ቤታቸው ሲያመ
ቡናና ሌላም የምግብ ዓይነት እየፈሰሰባቸው ብዙ ውዝግብ ፈጥረዋል ።
ችግር ለማቃለል የንብረት ክፍል ኃላፊዎች እንደ ተማሪዎች ብዛት ከሁ
ከሦስት ሳምንት በፊት ጀምሮ መጻሕፍት እንዲሸጡ ቢደረግና ተማሪዎችም
ብለው ት/ቤቱ ከመከፈቱ በፊት መጻሕፍታቸውን ገዝተው ቢቆዩ በጣም
ይሆናል ።

የመማሪያ መጻሕፍትን በሺያጭ መልክ ለተማሪዎች ማደል የሚሰጠው ጥ

፩/ የትምህርቱን ሥራ ለማፋጠን መጻሕፍት ከመምህራን ቀጥለው ያለ
ላጊ ረዳቶች ናቸው ። መጻሕፍት ያለው ተማሪ በቤቱም ፤ በት/ቤትም በበ
በሥራ ቀንም ሊያጠናና ሊያነብብ ይችላል ። የመማሪያ መጻሕፍት ለሽያጭ
ዋላቸው በፊት ለመምህራኑ መምሪያ ብቻ አንዳንድ መጻሕፍት እየተሰጡ ተማሪ

ዎቹ በጆሮአቸው በመስማትና ከስሌዳ በመገልበጥ በመሥራቱ የትምህርቱን እር ምጃ አንካሣ አድርጎት ነበር ።

፪/ ተገቢ መደርደሪያና የሠለጠኑ ሠራተኞች የሌሉአቸው ግምጃ ቤቶች መጻሕፍት በመሸጣቸውና ግምጃ ቤቱ በከፊል ባዶ በመሆኑ ሠራተኛው ለብዙ ጊዜ የታተሙትንና ብዙ ዓይነት ያላቸውን አሮጌ መጻሕፍት በማገላበጥ ከሚደርስበት የሥራ ብዛትና መጻሕፍቱ ቢጠፉ ከሚደርስበትም ዕዳ ይድናል ።

፫/ የተገዙት መጻሕፍት በገዙአቸው ሰዎች እጅ የመቆየት ዕድል ስላላቸው እነዚህ መጻሕፍት ሌሎችም ሰዎች እንዲያነብቡአቸው ይረዳሉ ።

፬/ ለአንድ ዓመት የታተሙት የመጻሕፍት ዋጋ ተመልሶ ስለሚገባና ለሚቀጥለውም ዓመት ማሳተሚያ ገንዘብ ስለሚገኝ በየትምህርት ቤቶች ገንኖ የነበረው የመማሪያ መጻሕፍት እጥረት ይቀንሳል ።

፭/ የትምህርት ሚኒስቴር የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ ቢያደርግና አዳዲስ የመማሪያ መጻሕፍትን ለወደፊቱ ማሳተም ቢፈልግ ቀድሞ የነበሩት አሮጌ መጻሕፍት ስለተሸጡ ፤ ለውጡ ቀላል ይሆናል ።

፮/ በየትምህርቱ ዘመን መጀመሪያና መጨረሻ መጻሕፍት ማደልና መሰብሰብ አስቸጋሪ የአስተዳደር ሥራ ስለሆነ መጻሕፍትን መሸጥ በዓመቱ መጀመሪያ ስለሚሠራ ቢያንስ በዓመቱ መጨረሻ በመጻሕፍት መሰብሰብ በኩል ያለውን ችግር ይቀንሳል ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚገኘው ጉዳይ ት/ቤቶች መጻሕፍት ሲያድሉ ተማሪዎቻቸው ይዘውባቸው ቢሄዱ ዕዳና ሌላም የነበረውን ጭቅጭቅ ያስቀራል ። አንዳንድ አስተማሪዎችም ለተማሪዎች አድሉ ተብለው የነበሩትን መጻሕፍት በዓመቱ መጨረሻ ባያስረክቡ የሚደርስባቸው ዕዳና ክስ ይቀርላቸዋል ።

፯/ ብዙ ልጆች ያሏቸው ወላጆች ለመጀመሪያው ልጅ የገዙአቸው መጻሕፍት ለሌሎች እንዲያገለግሉ ይጠቅማሉ ። ይህም ሲሆን እነዚህ ወላጆችና ልጆቻቸው የገዙአቸው መጻሕፍት ለሌሎች ልጆች እንደሚያገለግሉ ካወቁ በጥንቃቄ ይይዙአቸዋል ። በዚህም ሳቢያ ልጆቹ ለንብረት መጠንቀቅ ይማራሉ ።

የሚከተሉት ዘዴዎች በመጻሕፍት መሸጥ በኩል ያሉ ችግሮችን ሊያቃልሉ ይችላሉ ።

፩/ መጻሕፍትን በሚገባ መያዝ ከት/ሥራ አንዱ ስለሆነ በየት/ቤቱ ለሚገኙ የንብረት ክፍል ኃላፊዎች ስለመጻሕፍት አያያዝ አጭር ኮርስ ቢሰጥ ይረዳል ።

፪/ መጻሕፍት ለመሸጥ የተወሰኑ መምህራን ቢመደቡና ት/ቤት ሊከፈት ሁለትና ሦስት ቀን ሲቀረው መጻሕፍቱ እንዲሸጡ ቢደረግ የሕፃናት ትምህርት ጊዜ እንዳይባክን ይረዳል ።

፫/ ተማሪዎችና ወላጆቻቸው ት/ቤቱ ለክረምት ዕረፍት ከመዘጋቱ በፊት ለመስከረም የመጻሕፍት ዋጋ በቅድሚያ እንዲዘጋጁ ቢነገሩ ብዙዎቹ ተማሪዎች መጻሕፍቱን በሰዓቱ ለማግኘት ይችላሉ ።

፬/ ስለመጻሕፍቱ አሻሻጥ ጉዳይ ጉድለትና አለመግባባት እንዳይኖር መጻሕፍቱን የሚሸጡት መምህራንና ዲሬክተሩ ቀደም ብለው ስብሰባ ካደረጉ በኋላ የሚከተሉት ዘዴዎች ለሁሉም ሊታይ በሚቻልበት አኳኋን መግለጫ ሊሰጥ ይገባል ።